**GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA**
**Office of the Chief Financial Officer**
**Office of Tax and Revenue**

# የሲጋሬት፣ ሊትል ሲጋርና ሞዪስት ስናፍ ፍሎር ታክስ ሪተርን

## ተዘውትረው የሚጠይቁ ጥያቄዎች(ተ.የ.ጥ.)

**አዲሱ የሲጋራ ቀረጥ ምንድነው?መቼ ተግባር ላይ ይውላል?**

ከኦክቶበር 1, 2009 ጀምሮ የዲስሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሲጋራን ኤክሳይስ ቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ስጃራ ከ10¢ ወደ 12.5¢ ከፍ ያደርገዋል። ይህም አንድ 20 ሲጋራዎችን የያዘ ፓኮ ከ 2.00 ወደ $2.50 እንዲሁም አንድ 25 ሲጋራዎችን የያዘ ፓኮ ከ $2.50 ወደ $3.125 ሲሆን ይህም በDC ኮድ ሴክሽን 47-2402(a) እንደተገለጸው ነው።

**በሊትል ሲጋሮችና ሞዪስት ስናፍ ላይ የተበየነው አዲስት ታክስ ምንድነው? መቼ ነው ተግባራዊ የሚሆነው?**

ከኦክቶበር 1 2009 ጀምሮ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በ "ሊትል ሲጋርስን" እንዲሁም "ሞዪስት ስናፍ" ላይ ቀረጥ ማስከፈል ይጀምራል።

"ሊትል ሲጋር" ማለት፣ ፕሪምየም ሲጋር ያልሆነ፣ አንድ ሺ የሚሆን ከ 4 ½ ፓውንድ በላይ ክብደት ያለው ያሆነ ሲጋርን ያጠቃልላል። ሊትል ሲጋርን ለመሸጥ ወይም ባለቤት ለመሆን፣ ለእያንዳንዱ ሊትል ሲጋር 12.5¢ መከፈል ይኖርበታል። "ሞዪስት ስናፍ" ማለት፣ እንዲጨስና አፍንጫ ውስጥ ለመስገባት ተብሎ ያልተዘጋጀ፣ ያሆነ ደቆ የተከተፈ፣ የተፈጨ፣ ወይም ወደ ፓውደር የተቀየረ ትምባሆን ያመለክታል። የሞይስት ስናፍን ለመግዛት ወይም በንብረትነት ለመያዝ፣ ለእያንዳንዱ አውንስ 30¢ መክፈልና፣ ከአንድ አውንስ በታች ለሆኑ ደግሞ እንደየሚዛናቸው መጠን በተመሳሳይ ደረጃ ቀረጥ መክፈል ይኖርብዎታል።

## <u>ጅምላ ሻጮች/ቸርቻሪዎች/የቬንዲንግ ማሽ|ን ኦፐሬተሮች</u>

**ፍሎር ታክስ ምንድነው?**
ፍሎር ታክስ ማለት ቀደም ብሎ በአሮጌው ስሌት በተቀረጠው የሲጋራ ኢንቬንተሪ(ክምችት) ላይ ሲሆን ይህም ለደንበኛ ያልተሸጡትን ሊትል ሲጋሮችና ሞይስት ስናፎችን ማለት ነው። ፍሎር ታክስ የሚሰላው 50¢ ለ20 ሲጋራዎች ያለው ፓኮ እንዲሁም $62.5¢ ለ25 ሲጋራዎች ያለው ፓኮ በአሮጌው ስሌት፣ እንዲሁም 12.5¢ ለሊትል ሲጋር፣ እንዲሁም ለእያንዳንዱ የሞይስት ስናፍ አንድ አውንስ 30¢ እንዲሁም ከአንድ አውንስ በታች ለሆኑ ደግሞ እንደየሚዛናቸው መጠን በተመሳሳይ ደረጃ ቀረጥ ማለት ነው።

**የፍሎር ታክስ መክፈል ያለበት ማነ ነው?**

አዲሱ የኤክሳይስ ቀረጥ ክፍያ የሚመለከተው አስቀድሞ ማህተም የተደርገባቸውን የስጃራ ፍሎር ስቶኮች ይመለከታል። እንዲሁም በዲሲ በጅምላ ሻጮች እና ቸርቻሪዎች ለንግድ ማከፋፈል ወይም ለሽያጭ የተያዙትን በቬንዲንግ ማሺን ውስጥ ያሉትን ሲጋራዎችንና ሁሉንም ማህተም የተደርገባቸውን ሲጋራዎችን ያጠቃልላል። ቢሆንም፣ ሳብ-ሆልሴለሮችን ሳይጨምር፣ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ ጅምላ ሻጮች፣ ከዲስትሪክቱ ውጭ ባስቀመጧቸው የ"ሊትል ሲጋሮች" እና የ"ሞይስት ስናፍ" ላይ የተበየኑትን የፍሎር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የለባቸውም።

ከአዲሱ የኤክሳይስ ቀረጥ ክፍያ በተጨማሪ ቸርቻሪዎች በሁሉም ለተጠቃሚ የሚደረጉ ሽያጮች ላይ ከኦክቶበር 1 2009 ላይ ጀምሮ 6 ፐርሰንት የሽያጭ ቀረጥ መክፈል ይኖርባቸዋል። በትምባሆ ምርቶች ላይ የተበየነው የ 12 ፐርሰንት የሽያጭ ታክስ ላይ ምንም ለውጥ አልተደረገም።

**የወለል ቀረጥን (ፍሎር ታክስ) ሪተርን መቼ ነው የሚከፈለው?**

የስጃራ፣ ሊትል ሲጋርና ሞይስት ስናፍ ፍሎር ታክስ ሪተርን(FR-463) ለ Office of Tax and Revenue ከኦክቶበር 21, 2009 በፊት መስጠት አለበት። ክፍያዎትን በቼክ ወይም በማኒ ኦርደር ለ*D.C Treasurer* ተከፋይ ይሁን። በደብዳቤ የሲጋራ የታክስ ፍሎር ሪቱርኑን ክፍያ ወደ የሚከተለው አድራሻ ይላኩት፤ Office of Tax and Revenue, Audit Division, Cigarette Tax Enforcement Unit, P.O. Box 556, Washington, DC 20044

**የወለል ቀረጥን (ፍሎር ታክስ) ሪተርን ፋይል ካልተደረገና ታክስ እስከ ኦክቶበር 21 2009 ድረስ ካልተከፈለ ምን ይከተላል?**

የወለል ቀረጥን (ፍሎር ታክስ) ሪተርን ፋይል ካላደረጉና ታክስ እስከ ኦክቶበር 21, 2009 ድረስ ካልተከፈለ ታክስ አሴስመንት(ምርመራ) ይደርጋል። ቅጣቶችና ወለድ ከማስከተሉ በተጨማሪ በወንጀለኛነት ሊያስከስስዎት ይችላል። በተጨማሪ የያዙት የሲጋራ ላይሰንስ(ፍቃድ) ሊታገድብዎት ወይም ሊሰርዝብዎት ይችላል።

**ለሲጋራዎች ማስከፈል የሚችሉት አዲሱ ትንሹ ዋጋ ስንት ነው?**

ለማስከፈል የሚችሉት አዲሱ ትንሹ ዋጋ የሚወሰነው በአምራቹ የሲጋራዎች መሰረታዊ የፓኮ ዋጋ ላይ ተጨማሪ የ2 ፐርሰንት ለጅምላ ሻጮች እንዲሁም 8 ፐርሰንት ለቸርቻሪዎች የማንዳተሪ ማርክ አፕ ነው። የሲጋራ የጅምላ ሻጩ የማርክ አፕን መጠን ሲያሰላ የኤክሳይስ ታክስ ጭማሪ ከተደረገ በኋላ መሆን አለበት፤ ይህም የሲጋራው ምርት የሚሸጥበትን ትንሹ ዋጋን ለማዘጋጀት ነው።

## <u>የሲጋራ የጅምላ ሻጮች</u>

**የሲጋራ ጅምላ ሻጮች አልሸጥ ላሉ ሲጋራዎች እንዴት ነው ተጠያቂ የሚሆኑት?**

የሲጋራ ጅምላ ሻጭ አልሸጥ ያሉ ሲጋራዎች ለአምራቹ ከኦክቶበር 21 2009 በፊት እንደመለሰ ማሳወቅ ይኖርበታል። በዚህ ምክንያት፣ አልሸጥ ያሉ ሲጋራዎች ከኦክቶበር 21 2009 ጀምሮ በጅምላ ሻጩ ቅጥር ግቢ ውስጥ መገኘት የለባቸውም።

**በምን ምክኒያት የሲጋራ ጅምላ ሻጮች በትራንዚት(በሽግግር) ላይ ላሉ ሲጋራዎች ተጠያቂ ይሆናሉ?**

በትራንዚት(በሽግግር) ላይ ያሉና ወደ ገዢው ያልደረሱ ከኢንቬንተሪ ጋር አይጠቃለሉም።ነገር ግን ሽግግሩ በኢንቮይስ ወይም በቢል ኦፍ ሴይል መረጋገጥ አለበት። ተፈላጊው የድጋፍ ሰነድ ካልቀረበ ማንኛወም የሲጋራ ጅምላ ሻጭ ከኦክቶበር 1 2009 ጀምሮ በ "ሽግግር ላይ" ናቸው በሚባሉት ላይ የፍሎር ታክስ መክፈል ይኖርበታል።

**አዲሶቹን ስታምፖች ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ትሬዠሪ  መግዛት የሚቻለው መቼ ነው?**

አዲሱን የሲጋራ ታክስ ስታምፕስ ስሌት ሮሎስ ወይም ሽቶችን ከዲሲ ትሬዠሪ ከሴፕቴምበር 25, 2009 ጀምሮ መግዛት ይቻላል። እነዚህ ፓኮች ከኦክቶበር 1, 2009 በፊት የታተሙ ሊሆኑ የሚችሉ ቢሆንም ከዚህ ቀን አስቀድሞ መሸጥ የለባቸውም። እንደነዚህ አይነቶች የህግ ጥሰቶች ከታዩ የ ዲ.ሲ. ሲጋራ ህግ ቅጣት ይወስናል።

**ያሆኑ ጥያቄዎች ቢኖሩኝስ?**

**ማናችም ጥያቄዎች ቢኖረኝ ወይም ስለ ፍሎር ታክስ ሪተርን ተጨማሪ እገዛ ብፈልግ ማንን ነው የምጠይቀው?**

ማናቸውም ጥያቄ ቢኖርዎት ወይም ስለ ኤክሳይስ ታክስ ጭማሪ መስፈርቶችን በተመለከት ተጨማሪ እገዛ ቢፈልጉ ወደ ኦፊስ ኦፍ ታክስ ኤንድ ረቨኑ, ኦዲት ዲቪዠን በ (202) 442-6602 ይደውሉ ወይም ዌብሳይታችንን www.taxpayerservicecenter.com ይጎብኙ።